# ለተቀባዮችና ተንከባካቢዎች የቀረበ የመረጃ ቅጽ

## የኮሮና ቫይረስ በሽታ 2019ን (COVID-19) ለመከላከል የሞደርና (MODERNA) የCOVID-19 ክትባት እና ሞደርና (MODERNA) የCOVID-19 ክትባት ባይቫለንት/ BIVALENT (ኦሪጂናል እና ኦሚክሮን BA.4/BA.5) የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ

**ዕድሜያቸው ከ 6 ወራት እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ግለሰቦች**

**በSARS-CoV-2 ምክንያት የሚመጣውን የኮሮና ቫይረስ በሽታ 2019ን (COVID-19) ለመከላከል ልጅዎ የሚሰጠው ሞደርና (Moderna) የCOVID- 19 ክትባት፣ ወይም ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/Bivalent (ኦሪጅናል እና ኦሚክሮን BA.4/BA.5)፣ ከዚህ በኋላ ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) ተብሎ የሚጠራው ለልጅዎ ቀርበውለታል።**

**ይህ ለተቀባዮችና ተንከባካካዎች የቀረበ የመረጃ ቅጽ ዕድሜያቸው ከ 6 ወራት እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ለመጠቀም ፍቃድ የተሰጠውን የሞደርና (Moderna) የ COVID-19 ክትባትን እና ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) የተመለከተ መረጃ ይዟል።[1]**

**ሞደርና የCOVID- 19 ክትባት የሚከተሉት እንዲሰጥ የFDAን የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) አግኝቷል፥**

- **ዕድሜያቸው ከ 6 ወራት እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ሰዎች በሁለት ዶዝ የመጀመሪያ ተከታታይ ክትባት፤ እና**
- **ዕድሜያቸው ከ 6 ወራት እስከ 5 ዓመት ለሆኑ እና የሰውነታቸው የበሽታ መከላከል አቅም በተወሰነ ደረጃ ለተዳከመ ሰዎች ሶስተኛ የመጀመሪያ ተከታታይ ክትባት ለመስጠት።**

**ዕድሜያቸው ከ6 ወር እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ሰዎች የመጀመሪያውን ተከታታይ የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን ከወሰዱ ቢያንስ ከ 2 ወራት በኋላ ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (Bivalent) አንድ ኢጋዥ ዶዝ እንዲሰጥ የFDAን EUA አግኝቷል።**

**ሞደርና (Moderna) የ COVID-19 ክትባትን እና ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) ዕድሜያቸው ከ6 ወር እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ግለሰቦች ጥቅም ላይ እንዲውሉ በ FDA-አልተፈቀደላቸውም።**

ይህ የክትባት የመረጃ ቅጽ በአሁኑ ወቅት የCOVID-19 ወረርሽኝ በመከሰቱ ምክንያት ሊወስዱት ስለሚችሉት ስለ ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት እና የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) ክትባት ስጋቶችና ጥቅሞችን ለመረዳት የሚረዳዎ መረጃ ይዟል። ምንም አይነት ጥያቄ ካለዎት የልጅዎን የክትባት አገልግሎት ሰጪ ያነጋግሩ።

የሞደርና (Moderna) የCOVID-19ክትባት እና የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) ሁሉንም ሰው ላይከላከሉ ይችላሉ።

[1] የልጅዎ እድሜ 6 ዓመት የሞላ ቢሆንም እንኳ፣ ይህን የመረጃ ቅጽ ሊያገኙ ይችላሉ። በመጀመሪያው ዶዝ የወሰዱት ምንም አይነት ዶዝ ቢሆን፣ በሁለት ዶዞች በሚወስዱበት የጊዜ መካከል እድሜያቸው ከ5 ዓመት ወደ 6 ዓመት የሚቀየር ልጆች፣ (1) ዕድሜያቸው ከ 6 ወራት እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ግለሰቦች ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደውን የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን፤ ወይም (2) ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት እስከ 11 ዓመት ለሆኑ ግለሰቦች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተፈቀደላቸውን የሞደርና (Moderna) የ COVID-19 ክትባት መውሰድ ይችላሉ።

ይህ የመረጃ ቅጽ ማሻሻያ ሊደረግበት ይችላል። በጣም የቅርብ የመረጃ ቅጽ ለማግኘት እባክዎ www.modernatx.com/covid19vaccine-eua ን ይመልከቱ።

**ክትባቱን ልጅዎ ከመከተቡ በፊት ማወቅ ያለብዎ ነገር ምንድን**

**ነው COVID-19 ምንድን ነው?**

የCOVID-19 በሽታ SARS-CoV-2 ተብሎ በሚጠራ የኮሮና ቫይረስ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። ይህ አይነቱ የኮሮና ቫይረስ ከዚህ በፊት ታይቶ አያውቅም። በቫይረሱ ከተያዘ ከሌላ ሰው ጋር ንክኪ በማድረግዎ ምክንያት በCOVID-19 ሊያዙ ይችላሉ። በሽታው በዋናነት ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን ሊያጠቃ የሚችል የመተንፈሻ አካል ህመም ነው። በCOVID-19 የተያዙ ሰዎች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ ህመም የሚደርሱ የተለያዩ ምልክቶች እንደታዩባቸው ሪፖርት ተደርጓል። ምልክቶቹ ለቫይረሱ ከመጋለጥ በኋላ ከ2 እስከ 14 ቀናት ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ። ምልክቶቹ ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለትን፣ ሳልን፣ የትንፋሽ ማጠርን፣ ድካምን፣ የጡንቻ ወይም የሰውነት ህመምን፣ አዲስ የሚፈጠር የጣዕም ወይም ሽታ አለመለየትን፣ የጉሮሮ መሰርሰርን፣ የአፍንጫ ፈሳሽ መብዛትን፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስን፣ ተቅማጥን ሊይዙ ይችላሉ።

**ሞደርና (MODERNA) የCOVID-19 ክትባት፣ እና ሞደርና (MODERNA) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (BIVALENT) የሚገናኙት እንዴት ነው?**

ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) የተዘጋጀው ከ ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት ጋር በተመሳሳይ ዘዴ ነው፣ ነገር ግን በSARS-CoV-2 የኦሚክሮን (Omicron) ዝርያ ምክንያት የሚመጣውን የCOVID-19 በሽታን ለመከላከል የሚያገለግል የኦሚክሮን (Omicron) ንጥረ ነገር ይይዛል።

ስለ EUA ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በዚህ የመረጃ ቅጽ መጨረሻ ላይ "**የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ምንድን ነው?**" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

**ልጅዎ ከእነዚህ ክትባቶች የትኛውንም ከመውሰዱ በፊት ለልጅዎ ክትባት አቅራቢ መግለጽ ያለብዎ ምንድን ነው?**

ለልጅዎ ክትባት አቅራቢዎ የሚከተሉትን ጨምሮ ስለ ሁሉም የልጅዎ የጤና ሁኔታዎችዎ ይንገሩት:

- የትኛውም አላርጂዎች ካለበት
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) ያለበት ከሆነ
- ትኩሳት ካለበት
- የደም መፍሰስ ችግር ወይም የደም መቅጠን ካለበት
- የበሽታ መከላከል አቅሙ የተዳከመ ከሆነ ወይም የልጅዎ የበሽታ መከላከል ስርአቱ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር መድሀኒት እየወሰደ ከሆኑ
- ሌላ የCOVID-19 ክትባት ከወሰደ
- ከክትባት ጋር በተያያዘ እራሱን ስቶ የሚያውቅ ከሆነ

**ሞደርና (MODERNA) የCOVID-19 ክትባትን፣ ወይም ሞደርና (MODERNA) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (BIVALENT) መውሰድ የሌለበት ማን ነው?**

በሚከተሉት ሁኔታዎች ልጅዎ ከእነዚህ ክትባቶች አንዱንም መውሰድ የለበትም፥

- ቀደም ሲል የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን ዶዝ ከወሰደ በኋላ ከባድ አለርጂ ካጋጠመው
- በእነዚህ ክትባቶች ባሉ በየትኛውም ግብአት ምክንያት ከባድ አለርጂ አጋጥሞ ከነበረ

**የእነዚህ ክትባቶች ግብዓቶች ምንድን ናቸው?**

የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት እና የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (Bivalent) የመሚከተሉትን ግብአቶች ይይዛሉ፡ ሜሴንጀር ሪቦኒውሴሊክ አሲድ (mRNA)፣ ሊፒዶች (SM-102, ፖሊቲሊን ግሊኮል [PEG] 2000 ዲሚሪስቶይል ግሊሴሮል [DMG]፣ ኮሌስትሮል እና 1,2-distearoyl-sn-glycero-3-ፎስፎኮሊን [DSPC])፣ ትሮሜታሚን፣ ትሮሜታሚን ሀይድሮክሎራይድ፣ አሴቲክ አሲድ፣ ሶዲየም አሴቴት ትራይሀይድሬት፣ እና ስኳር።

**እነዚህ ክትባቶች የሚሰጡት እንዴት ነው?**
የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት እና ወይም የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (Bivalent) ለልጅዎ በመርፌ መልኩ በጡንቻው ላይ ይሰጡታል።

<u>የመጀመሪያ ክትባት:</u> የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት በአንድ ወር ልዩነት በ2 ተከታታይ ዶዝ ይሰጣል። የተወሰኑ አይነት የበሽታ መከላከል አቅም ችግሮች አሉባቸው ተብሎ ለሚወሰን ሰዎች ሁለተኛውን ዶዝ ከወሰዱ ቢያንስ ከ 1 ወር በኋላ ሶስተኛው የመጀመሪያ ዶዝ ክትባት ሊሰጣቸው ይችላል።

<u>አጋዥ ዶዝ:</u> የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (Bivalent) የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት የመጀመሪያውን ተከታታይ ክትባት ከተጠናቀቀ ቢያንስ ከ 2 ወራት በኋላ በአንድ አጋዥ ዶዝ ይሰጣል።

**እነዚህ ክትባቶች ከዚህ ቀደም ጥቅም ላይ ውለው ያውቃሉ?**
በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዕድሜያቸው 6 ወራት እና ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎች በEUA ስር የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን ወስደዋል። በህክምና ሙከራዎች ወደ 5,000 የሚጠጉ እድሜያቸው ከ 6 ወራት እስከ 5 ዓመት የሆኑ ሰዎች የክትባቱን ቢያንስ 1ዱን የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት ወስደዋል። በሌሎች ክሊኒካል ሙከራዎች ደግሞ፣ ወደ 4,000 የሚጠጉ እድሜያቸው ከ 6 ዓመት እስከ 11 ዓመት የሆኑ ሰዎች እና እድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ 30,000 ሰዎች ቢያንስ 1 የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት ዶዝን ወስደዋል።

በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዕድሜያቸው 6 ወራት እና ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎች በEUA ስር የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (Bivalent) (ኦሪጅናል እና ኦሚክሮን BA.4/BA.5) ወስደዋል። በህክምና ሙከራ ወቅት ወደ 400 የሚጠጉ እድሜያቸው 18 አመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በተለየ የኦሚክሮን/ Omicron ንጥረ ነገር ይዘቱ ከሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent የሚለየውን የባይቫለንት ክትባት 1 ዶዝ ወስደዋል።

**እነዚህ ክትባቶች የሚያስገኟቸው ጥቅሞች ምንድን ናቸው?**
የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት COVID -19ን እንደሚከላከል ታይቷል። FDA በSARS-CoV-2 የኦሚክሮን ዝርያ ምክንያት የሚመጣውን የCOVID-19 በሽታ በተሻለ ሁኔታ ለመከላከል የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት/ Bivalent ጥቅም ላይ እንዲውል ፈቅዷል።

የክትባቱ ከCOVID-19 መከላከል የቆይታ ጊዜ በአሁኑ ወቅት አልታወቀም።

**የእነዚህ ክትባቶች ስጋቶች ምንድን ናቸው?**
ክትባቱ ከባድ አለርጂ የሚያስከትልበት አጋጣሚ በጣም ጥቂት ነው። ከባድ አለርጂ በዋናነት የሚያጋጥመው አንድ ዶዝ ከተወሰደ በኋላ ካሉት ጥቂት ደቂቃዎች ጀምሮ እስከ አንድ ሰአት ያክል ነው። በዚህም ምክንያት የልጅዎ ክትባት አቅራቢ የክትባቱን ሁኔታ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ልጅዎ ክትባቱን በወሰደበት ቦታ እንዲቆይ ሊጠይቀው ይችላል። የከባድ አለርጂ ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡
- የመተንፈስ ችግር
- የፊት ወይም ጉሮሮ እብጠት
- የልብ ምት መፍጠን
- ከባድ የሙሉ ሰውነት መንደብደብ
- መደበትና ድካም

ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) በጥቂት የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት እና የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) ክትባቶችን በወሰዱ ሰዎች ላይ ተስተውለዋል። በእነዚህ አብዛኞቹ ሰዎች ላይ ምልክቶቹ መታየት የጀመሩት ክትባቱን በወሰዱ በጥቂት ናት ውስጥ ነው። ይህ የሚያጋጥምበት እድል በጣም ዝቅተኛ ነው። ልጅዎ ክትባቱን ከወሰደ በኋላ፣ በተለይም የክትባቱን ዶዝ ከወሰደ በኋላ ባሉት 2 ሳምንታት ውስጥ የትኛውም የሚከተሉት ምልክቶች ከታዩበት ወዲያውኑ የህክምና ክትትል ያድርጉ፡

- የደረት ህመም
- ትንፋሽ ማጠር ወይም የመተንፈስ ችግር
- የፈጣን አተነፋፈስ፣ የልብ መርገብገብ ወይም መውጋት ስሜት
- እራስን መሳት
- ያልተለመደ እና የማያቋርጥ ብስጩነት
- ያልተለመደ እና የማያቋርጥ ዝቅተኛ የሆነ አመጋገብ
- ያልተለመደ እና የማያቋርጥ ድካም እና የአቅም ማነስ
- የማያቋርጥ ማስመለስ
- የማያቋርጥ የሆድ ህመም
- ያልተለመደ እና የማያቋርጥ ቀዝቃዛ የሆነ የገረጣ ቆዳ

በእነዚህ ክትባቶች የህክምና ሙከራዎች ሪፖርት የተደረጉት የጎኒዮሽ ውጤቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡

- ክትባቱ የሚሰጥበት የሰውነት ክፍል አካባቢ የሚፈጠሩ አሉታዊ ምላሾች፡ ህመም፣ ክትባቱ የሚሰጥበት እጅ የብሽሽት ክፍል መቆጣትና እብጠት፣ መቅላት፣ እና እብጠት (የሰውነት መደደር)
- ጠቅላላ አሉታዊ ምላሾች፡ ድካም፣ ራስ ምታት፣ የጡንቻ ህመም፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ማቅለሽለሽና ማስመለስ፣ ትኩሳት፣ የመገጣጠሚያ ህመም፣ የሰውነት መቆጣት/ማልቀስ፣ እንቅልፍ ማጣት እና የምግብ ፍላጎት ማጣት

የመጠቀም ፍቃድ መሰጠት በኋላ ሪፖርት የተደረጉት የጎኒዮሽ ውጤቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡

- ከባድ አለርጂ
- ዩሪቲካሪያ (የሚያሳክ ሽፍታ)
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት)
- ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት)
- ከክትባቱ ጋር በተያያዘ እራስዎን ስተው ያውቁ ከሆነ

እነዚህ ሁሉም በአንድ ጊዜ የሚያጋጥሙ የእነዚህ ክትባት የጎኒዮሽ ውጤቶች ላይሆኑ ይችላሉ። ከባድና ያልተጠበቁ የጎኒዮሽ ውጤቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። እነዚህ ክትባቶች ሊያስከትሏቸው የሚችሏቸው የጎኒዮሽ ውጤቶች አሁንም በመጠናት ናቸው።

**የጎኒዮሽ ውጤቶች ካጋጠሙኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ልጅዎ ከባድ አለርጂ ካጋጠመው ወደ 9-1-1 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ሆስፒታል ይሂዱ።

የትኛውም ልጅዎን የሚያሳስብ ወይም የማይጠፉ የጎኒዮሽ ውጤቶች ካጋጠመው ለክትባት አቅራቢው ወይም ለልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ይደውሉ።

የክትባቱን የጎኒዮሽ ውጤቶች ለ**FDA/CDC የክትባት አሉታዊ ክስተት ሪፖርት ማቅረቢያ ሲስተም (VAERS) ሪፖርት ያድርጉ**። የVAERS የነጻ ጥሪ መስመር 1-800-822-7967 ነው ወይም በኦንላይን በ https://vaers.hhs.gov/reportevent.html ሪፖርት ያድርጉ። እባክዎ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅጹ በሳጥን #18 ስር በሚገኘው የመጀመሪያው መስመር ላይ እንደተስማሚነቱ ወይም “የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት EUA” ወይም "የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት ባይቫለንት (Bivalent) EUA" የሚለውን ያካቱ።

ከዚህ በተጨማሪም የጎኒዮሽ ውጤቶችን ለModernaTX.Inc በ1-866 MODERNA (1-866-663-3762) ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

በተጨማሪም በ **v-safe የሚመዘገቡበት አማራጭም ሊሰጥዎ ይችላል። V-safe** የCOVID-19 ክትባትን ከወሰዱ ሰዎች ስላጋጠሟቸው የጎኒዮሽ ውጤቶች ለማረጋገጥ የጽሁፍ መልእክትና የድረገጽ ጥናቶችን የሚጠቀም የፍቃደኝነት ስማርት ስልክን መሰረት ያደረገ መሳሪያ ነው። **V-safe** ለCDC ስለ COVID-19 ክትባቶች አስተማማኝነት ለመቆጣጠር የሚረዱትን ጥያቄዎች ይጠይቅዎታል። **V-safe** በተጨማሪም አስፈላጊ ከሆነ የዶዝ ማስታወሻ ይሰጣል እንዲሁም ተሳታፊዎች የCOVID-19 ክትባትን መውሰዳቸውን ተከትሎ ከባድ የጤና ተጽእኖ እንደተፈጠረባቸው ሪፖርት የሚያደርጉ ከሆነ የቀጥተኛ የCDC የስልክ ክትትል ያደርጋል። እንዴት እንደሚመዘገቡ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት: www.cdc.gov/vsafeን ይጎብኙ።

### የሞደርና (MODERNA) የCOVID-19 ክትባት ወይም የሞደርና (MODERNA) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (Bivalent) ልጄ እንዳይወስድ ብወስን ምን ይሆናል?
በ EUA ስር፣ ክትባቱን ለመውሰድ ለመስማማት ወይም ለመቃወም የቀረበ አማራጭ አለ። ከእነዚህ ክትባቶች የቱንም ልጅዎ እንዳይወስድ ቢወስኑ የልጅዎን መደበኛ የህክምና እንክብካቤ ላይ ለውጥ አይፈጥርም።

### COVID-19ን ለመከላከል በሞደርና (Moderna) ወይም በሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (Bivalent) ምትክ የሚቀርቡ ሌሎች አማራጮች አሉ?
ዕድሜያቸው ከ6 ወር እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ህጻናት የመጀመሪያ ክትባት፣ COVID-19ን የሚከላከሉ ሌሎች ክትባቶች በEUA ስር ሊኖሩ ይችላሉ። ዕድሜያቸው 5 ዓመት የሆኑ የመጀመሪያ ክትባታቸውን በማንኛውም በ FDA የተፈቀደ የCOVID-19 ክትባት ላጠናቀቁ ህጻናት፣ በኢጋዝ ዶዝነት በ EUA ስር ሌሎች የ SARS-CoV-2 የኦሚክሮን (Omicron) ንጥረ ነገር የያዙ ሌሎች ባይቫለንት ክትባቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ዕድሜያቸው ከ6 ወር እስከ 4 ዓመት የሆኑ የመጀመሪያ ክትባታቸውን በሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት ላጠናቀቁ ህጻናት፣ በኢጋዥ ዶዝነት በ EUA ስር የሚገኘው ብቸኛው ክትባት የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (Bivalent) ነው።

### ልጄ የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን ወይም የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (BIVALENT)ን ከሌሎች ክትባቶች ጋር በተመሳሳይ ጊዜ መውሰድ ይችላል?
የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን ወይም የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንትን (Bivalent) በተመሳሳይ ጊዜ ከሌላ ክትባት ጋር አብሮ መስጠትን በተመለከተ እስከ አሁን ድረስ ለFDA ዳታ አልቀረበም። የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን ወይም ሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት፣ ባይቫለንት (BIVALENT)ን ከሌሎች ክትባቶች ጋር አብሮ ልጅዎ እንዲወስድ ካሰቡ በአማራጮችዎ ላይ ከልጅዎ ጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ይወያዩ።

### የልጄ በሽታ መከላከል አቅም የተዳከመ ከሆነ ምን ይሆናል?
የልጅዎ በሽታ መከላከል አቅም የተዳከመ ከሆነ፣ የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን ሶስተኛውን ዶዝ ለልጅዎ እንዲወስድ የማድረግ እድሉ ይሰጥዎታል። በሽታ መከላከል አቅማቸው የተዳከመና ዕድሜያቸው ከ6 ወር እስከ 5 ዓመት የሆኑ የመጀመሪያ ክትባታቸውን በሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባትን፣ ባይቫለንት (Bivalent) ያጠናቀቁ ህጻናት አንድ የሞደርና (Moderna) የCOVID-19 ክትባት ኢጋዥ ዶዝ ሊወስዱ ይችላሉ። ክትባቶቹ የበሽታ መከላከል አቅማቸው ለተዳመ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ከCOVID-19 ላይከላከሉ ስለሚችሉ፣ COVID-19ን ለመከላከል እንዲረዳው ልጅዎ አካላዊ ጥንቃቄዎችን መከተሉን መቀጠል አለበት። ከልጅዎ ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ሰዎች እንደአስፈላጊነቱ መከተብ አለባቸው።

### እነዚህ ክትባቶች ልጄን COVID-19 ሊያስዙት ይችላሉ?
አይ። እነዚህ ክትባቶች SARS-CoV-2 የማይይዙ በመሆኑ ልጅዎን COVID-19 ሊያሲዙ አይችሉም።

**የልጅዎን ክትባት ካርድ ይያዙ**
ልጅዎ የመጀመሪያውን የCOVID-19 ክትባት ሲወስድ የክትባት ካርድ ይሰጥዎታል። ተመልሰው በሚመጡበት ወቅት ካርዱን መያዝዎን አይርሱ።

**ተጨማሪ መረጃ**
ጥያቄዎች ካሉዎ ከዚህ በታች የተገለጸውን ድረገጽ ይጎብኙ ወይም ከታች በተገለጸው ስልክ ቁጥር ይደውሉ።

በጣም የቅርብ የመረጃ ቅጾችን ለማግኘት እባክዎ ከዚህ በታች የቀረበውን የQR ኮድ ስካን ያድርጉ።

| **የሞደርና (Moderna) Covid-19 ድረገጽ** | **ስልክ ቁጥር** |
|---|---|
| www.modernatx.com/covid19vaccine-eua | 1-866-MODERNA<br>(1-866-663-3762) |

**ተጨማሪ መረጃ እንዴት አገኛለሁ?**

- የክትባት አቅራቢውን ይጠይቁ።
- CDCን በ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/index.html ይጎብኙ።
- FDAን በ https://www.fda.gov/emergency-preparedness-and-response/mcm-legal-regulatory-and-policy-framework/emergency-use-authorization ይጎብኙ።
- የግዛትዎን የአካባቢዎን ወይም የማህበረሰብ ጤና መምሪያ ያነጋግሩ።

**የልጄ የክትባት መረጃ የት ይመዘገባል?**
ክትባት አቅራቢው የልጅዎን የክትባት መረጃ በግዛት/አካባቢ የክትባት መረጃ ሲስተም (IIS) ወይም ሌላ የተመደበ ሲስተም ላይ ሊያካትት ይችላል። ስለ IISዎች የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት: https://www.cdc.gov/vaccines/programs/iis/about.htmlን ይጎብኙ።

**እነዚህን የCOVID-19 ክትባቶች ለማግኘት የመከተቢያ ክፍያ እከፍላለሁ?**
አይ። በአሁኑ ወቅት ክትባት አቅራቢው የክትባቱን ዶዝ ለመስጠት ሊያስከፍልዎ የማይችል ከመሆኑም በተጨማሪ የሚወስዱት የCOVID-19 ክትባትን ብቻ ከሆነ ለክትባቱ መውሰጃ ክፍያ ወይም የትኛውም ሌላ ክፍያ ከኪስዎ አይከፍሉም። ሆኖም የክትባት አቅራቢዎች ለክትባቱ ወሳጆች የCOVID-19 ክትባት መስጫ ክፍያዎች ሽፋን ከሚሰጥ ፕሮግራም ወይም እቅድ (የግል የመድን ዋስትና፣ Medicare፣ Medicaid፣ የመድን ዋስትና ላልተገባላቸው ተቀባዮች HRSA COVID-19 Uninsured Program ፕሮግራም) ተገቢውን መልሶ ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ።

**የሚጠረጠሩ የማጭበርበር ጉዳዮችን የት ሪፖርት ማድረግ እችላለሁ?**
የCDC የCOVID-19 ክትባት ፕሮግራም መስፈርቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ስለ የትኛውም ጥሰቶች የሚያውቁ ግለሰቦች እነዚህን ለዩኤስ የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፣ የዋና መርማሪ ጽ/ቤት በ1-800-HHS-TIPS ወይም TIPS.HHS.GOV ሪፖርት እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

**የጉዳት የአጸፋ እርምጃዎች የካሳ ፕሮግራም ምንድን ነው?**
የጉዳት የአጸፋ እርምጃዎች የካሳ ፕሮግራም (CICP) እነዚህን ክትባቶች ጨምሮ በተወሰኑ መድሀኒቶች ወይም ክትባቶች የተነሳ ከባድ ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች የሚከፍሏቸው የህክምና እንክብካቤ ወጪዎች እና ሌሎች ልዩ ወጪዎች እንዲከፈሏቸው የሚያግዝ የፌደራል ፕሮግራም ነው። በጠቅላላው የካሳ ጥያቄው ክትባቱ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በአንድ (1) አመት ውስጥ ለCICP መቅረብ አለበት። ስለዚህ ፕሮግራም የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.hrsa.gov/cicp/ ን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 1-855-266-2427 ይደውሉ።

**የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ምንድን ነው?**
የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) እንደ የወቅቱ የCOVID-19 ወረርሽኝ የመሳሰሉ የማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ወቅ ክትባቶችን ጨምሮየህክምና ምርቶች እንዲቀርቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያመቻች አሰራር ነው። EUA በCOVID-19 ወረርሽኝ ቆይታ ውስጥ ለአስቸኳይ ጊዜ መድሀኒቶችን እና የባዮሎጂካል ምርቶችን ለመጠቀም አሳማኝ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ይህን በሚፈቅደው የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች ጽ/ቤት (HHS) መግለጫ ድጋፍ አግኝቷል። በአስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ የተሰጠው ምርት ከ FDA ፍቃድ ካገኘ ምርት ጋር በ FDA አንድ አይነት የግምገማ ሂደት አይደረግለትም።

FDA የተወሰኑ መስፈርቶች ሲሟሉ EUA ሊሰጥ የሚችል ሲሆን መስፈርቶቹ በቂ፣ የተፈቀዱ፣ ዝግጁ አማራጮች አለመገኘትን ይይዛሉ። በተጨማሪም የFDA ውሳኔ በሚቀርቡለት ምርቱ በCOVID-19 ወረርሽኝ መከሰት ወቅት COVID-19ን ለመከላከል ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል እና የምርቱ የታወቁና ሊሰሩ የሚችሉ ጥቅሞችን እና ከምርቱ የታወቁና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች ይልቅ ጥቅሞቹ እንደሚያመዝኑ በሚያሳዩ ሳይንሳዊ ማስረጃዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ይመሰረታል። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት ምርቱ ጥቅም ላይ እንዲውል እነዚህ ሁሉ መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው።

ካልተቋረጠ ወይም ካልተሻረ በስተቀር (ይህ ከሆነ ግን፣ ከዚያን ጊዜ በኋላ ምርቱ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም)፣ የ ኮቪድ-19 የ EUA አስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ አሰፈላጊነት እስካለ ድረስ፣ የዚህን ምርት EUA ተግባራዊ እንደሆነ የሚቆይ ይሆናል።

Moderna US, Inc.
Cambridge, MA 02139

©2022 ModernaTX, Inc. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።
የፈጠራ ባለቤትነት(ቶች): www.modernatx.com/patents
የተሻሻለበት ቀን: ታህሳስ/7/2022 ዓ.ም

ይህ የመረጃ ቅጽ ለኤሌክትሮኒክ የሕክምና መረጃዎች/የክትባት የመረጃ ሲስተሞች ለክትባት ተቀባዩ የቀረበ መሆኑን ለማረጋገጥ ስካን ያድርጉ።

GDTI: 0886983000516